Seattle
Office of Planning & Community Development

# አንድ ሲያትል
# የአጠቃላይ ዕቅድ ዋና ዋና ማሻሻያ

የሲያትል አጠቃላይ ዕቅድ ከተማችን እንዴት እንደምታድግ እና ኢንቨስትመንቶችን እንደምታካሂድ የተመለከተ መመሪያ ነው። እቅዱ መኖሪያ ቤቶችና የስራ ቦታዎች የት መሰራት እንዳለባቸው እና የት ለትራንስፖርት፣ አገልግሎቶች፣ ፓርኮችና ሌሎች የህዝብ ንብረቶች ላይ ኢንቨስት ማድረግ እንዳለብን በተመለከተ ለሚተላለፉ ውሳኔዎች በመመሪያነት ያገለግላል። ግባችን ከተማውን ለአሁን ማህበረሰቦችም ሆነ ለወደፊት ነዋሪዎች የበለጠ እኩልነት ያለበት፣ ለኑሮ አመቺ፣ ዘላቂና ለመቋቋም ዝግጁ ማድረግ ነው።

የተሻሻለው እቅዳችን ለአዲስ እና ነባር ተግዳሮቶች ማለትም፡ የዘር ዕኩልነት፣ የመኖሪያ ቤት ወጪዎች፣ ለኢኮኖሚያዊ ዕድልና ትምህርት ተደራሽ መሆን፣ የአየር ንብረት ለውጥ እና ሌሎችም ምላሽ ይሰጣል። የተለያዩ የእድገትና ኢንቨስትመንት አቀራረቦችን የመፈናቀል ጫናዎችን ከሚቀንሱ አዳዲስ ስትራቴጂዎች ጋር አብረን እናጠናለን።

**መኖሪያ ቤት**

**የስራ ዕድሎች/ ኢኮኖሚ**

**ትራንስፖርት**

**የአካባቢ ፍትህ/ የአየር ንብረት ለውጥ**

**ፓርኮች/ ክፍት ቦታዎች**

**ለኑሮ አመቺነት**

## የእርስዎ ድምጽ እቅዱን ቅርጽ ያስይዘዋል

ከተማው የእቅዱን ረቂቅ በማዘጋጀት ረገድ የሁሉንም ነዋሪዎች ግብዓት ለማግኘት ይጠይቃል። ስለ ከተማው ያልዎትን ራዕይ ለማጋራት እንዲቀላቀሉን እንጋብዝዎታለን። ወቅታዊ መረጃዎችን ለማግኘት በ www.seattle.gov/opcd በመመዝገብ ተጨማሪ ማወቅ፣ የመነሻ መረጃና ዳታ ማግኘት እና በተሳትፎዎ መቀጠል ይችላሉ።

እንደ ከተማ ያለፉትን እቅዶች ጎጂ ነገሮች ለመጠገን እና ለወደፊት ለሁሉም ሰው ዕኩልነት የሰፈነበት ሁኔታን ለማሳካት ለመስራት ቁርጠኞች ነን። ይህን ለማሳካትም የእቅድና ማህበረሰብ ልማት ቢሮ (OPCD) የጥቁሮችን፣ ነባር ተወላጆችና የተለየ ቀለም ያላቸው ማህበረሰቦችን እንዲሁም በእቅድ ዝግጅት አሰራሮች ውስጥ የተዘነጉ የሌሎች ማህበረሰቦች ድምጾችን ማዕከል ያደርጋል። ይህ ቁርጠኝነት በOPCD እኩል የማህበረሰብ ተሳትፎ ፍልስፍናዎች ውስጥ ተካቷል (seattle.gov/opcd/about-us)።

## የፕሮጀክት የጊዜ ሰሌዳ

2022 | እሩብ ዓመት 2 | እሩብ ዓመት 3 | እሩብ ዓመት 4 | 2023 | እሩብ ዓመት 2 | እሩብ ዓመት 3 | እሩብ ዓመት 4 | 2024 | እሩብ ዓመት 2 | እሩብ ዓመት 3

**የፕሮጀክት ትግበራ**
የፕሮጀክቱ መነሻና የማህበረሰብ ተሳትፎ መሳሪያዎች ዝግጅትና ማጋራት

**ዕቅዱን ቅርጽ ማስያዝ**
ዋና ዋና ጉዳዮችን እና ሊሳኩ የሚችሉ የእድገት ስትራቴጂዎችን ለይቶ ማስቀመጥ

**የእቅዱን ረቂቅ ማዘጋጀት**
የማህበረሰብ ግብዓት ትንተና እና የግቦችና ፖሊሲዎች ትንተና

**ምርመራ + ማጥራት**
በእድገት ስትራቴጂዎቹ ትንተናና ረቂቅ እቅዱ ላይ መደበኛ የህዝብ አስተያየት መቀበል

**የመጨረሻ እቅድ + ዞን መከለል**
የከንቲባውን እቅድ ከተመራጩ የእድገት አማራጭ እና የዞን ክለላ ህግ ጋር ማጠናቀቅ

**እቅዱን ማጽደቅ**
የመጨረሻ እቅዱ በከተማ ካውንስሉ መመርመር፣ መፈቀድና ትግበራ

## ለተጨማሪ መረጃ፥

seattle.gov/opcd
@SeattleOPCD
fb.com/seattleopcd

## ግብረ መልስ ይስጡ + ተጨማሪ ይወቁ:

ስካን ያድርጉ

## ለግንኙነት/ያነጋግሩን፥

Michael Hubner
michael.hubner@seattle.gov

ይህን ሰነድ በተለዋጭ ፎርማት ወይም ቋንቋ ለማግኘት Bernardo Sernaን በ bernardo.serna@seattle.gov ያነጋግሩ።


# የእድገት ስልት

## የዛሬው የከተማ መንደር የእድገት ስልት

የአጠቃላይ ዕቅዱ የዕድገት ስልት በሚቀጥሉት 20 ዓመታት ውስጥ የሚገነባው ለኑሮ ኣስፈላጊ የሆኑ የአካባቢ ልማት እና መዋዕለ ንዋዮች እንዴት በዝግመተ-ለውጥ እንደሚሻሻሉ እና የሚጠበቀውን የህዝብ ቁጥር እንዴት ማቀፍ እንደሚችሉ እና የስራ እድገት ለማስተናገድ እና የከተማውን ግቦች ለማሳካት የከተማው ራዕይ ነው። ሲያትል በ2050 ወደ አንድ ሚሊዮን የሚጠጉ ሰዎች የሚኖሩባት ከተማ እንደምትሆን ትንበያዎች ያመለክታሉ። የዕድገት ስልታችንን ማዘመን የመኖሪያ ቤቶች አቅርቦት፣ ብዝኅነት፣ እንዲሁም ተመጣጣኝነት ያለው የቤት ዋጋን ይደግፋል። የበለጠ ፍትሃዊ እኩልነት እና ዘላቂነት ያለው ከተማ ለመሆን አላማችን እናደርጋለን።

የእድገት ስልት ቅርጾች:

- የመኖሪያ፣ የንግድ፣ እና የኢንዱስትሪያዊ ልማት የት እንደምንፈቅድ
- የተፈቀዱት አዳዲስ የመኖርያ ቤቶች ዓይነቶች (አፓርታማዎች፣ የከተማ ቤቶች፣ የማይገናኙ ቤቶች)
- በማህበረሰብ መገልገያዎች ምቾት እና ፀረ-መፈናቀል እርምጃዎች ላይ እንዴት መዋዕለ ንዋይ እንደምናደርግ




የከተማ መንደር ስልት እድገት ላይ በማተኮር ተሳክቶለታል። ባለፉት አስርት አመታት፣ በከተማው ውስጥ ያሉት 83% አዳዲስ ቤቶች – በአብዛኛው ትናንሽ አፓርታማዎች – የታመቁ፣ በእግር መደረስ በሚችሉ፣ እና በሕዝብ መጓጓዣ የተገናኙ የሰፈሮች ድብልቅ ጥቅም የተገነቡ ናቸው።

ነገር ግን፣ ብዙዎች ከከተማ መንደሮች ውጭ ያሉ ሰፈሮች ጥቂት በዋጋ ተመጣጣኝ የመኖሪያ ቤት አማራጮች ያሏቸው እና በከተማው ውስጥ ሁሉ ዋጋዎቻቸው በከፍተኛ ደረጃ የጨመሩ ናቸው። የቤተሰብ መጠን እና የባለቤትነት አማራጮች ለብዙዎች ተደራሽ አይደሉም።

አሁን በቅርብ ጊዜ በከተማው የተካሄደው የዘር ፍትሃዊ እኩልነት ትንተና የከተማ መንደር ስልት መገለልን በአንድ ታሪካዊ ስርዓተ-ጥለት መንገድ እንደሚያስቀጥል እና በቀለም ማህበረሰቦች ላይ የሚደርሰውን የመፈናቀል ጫና እንደሚጨምር አረጋግጧል።

### የእድገት ስልቱን ማዘመን ለሚከተሉት ይረዳናል፥

- በከተማው ውስጥ ለበለጠ የመኖሪያ ቤት አቅርቦት እና ምርጫ መፍቀድ
- የበለጠ በዋጋ ተመጣጣኝ ቤቶችን መደገፍ
- የአድልዎ ታሪካችንን መነጋገር/ መፍታት እና የመፈናቀል ጫናን መቀነስ
- ከአዳዲስ የሕዝብ መጓጓዣ የመዋዕለ ንዋዮች ፍሰት አጠገብ ተጨማሪ የመኖርያ ቤቶች እንዲኖሩ ማበረታታት
- ለአየር ንብረት ለውጥ ምላሽ መስጠት እና በመኪናዎች ላይ ያለ ጥገኛነትን መቀነስ

# የአካባቢያዊ ተጽዕኖ መግለጫ

እንደ አንድ የአካባቢ ተጽዕኖ መግለጫ (EIS) አካል በመሆን ለእድገት የተለያዩ አቀራረቦችን ጥቅሞች እና ተፅእኖዎችን እናጠናለን። በሕዝብ ተሳትፎ በኩል ሰፊ ዝርጊያ ያላቸው የምንሰማቸውን ሃሳቦች የሚያንፀባርቁ ሰፋ ያሉ አማራጮችን ለማጥናት እና በሚቀጥለው የእቅዱ ማሻሻያ ሂደት ወቅት ለተመረጡት ባለስልጣናት ተለዋዋጭነትን ለመስጠት እያቀድን ነው።


አንድ የአካባቢ ተጽዕኖ መግለጫ (EIS) ረቂቅ በ2023 መኸር ወቅት ለህዝብ ግምገማ እና አስተያየት ይቀርባል። በ2024 ሊጠናቀቅ የሚጠበቀው የመጨረሻው የዕድገት ስልት፣ ከስልቶቹ እና ከሚቀርቡ አማራጭ አካባቢዎች/ አድራሻዎች ውስጥ የተውጣጣ ድብልቅ አቀራረብ እንደሚሆን ይጠበቃል።

### አማራጭ 1: ምንም የሚወሰድ ድርጊት የለም

አሁን ያለውን ነባሩን የከተማ መንደር ስልታችንን እንደ አንድ የንጽጽር መነሻ እናጠናለን።

### አማራጭ 2: ያተኮረ

አሁን ባሉ ነባር የንግድ ወረዳዎች ዙሪያ ማዕከል ያደረጉ **የሰፈር መልህቆች/ የተጀቡ የሰፈር ኪሶች** በሚባሉ አዳዲስ አካባቢዎች የመኖሪያ ቤት ተጨማሪ እድሎች ማስፋት





**የጐረቤት መልህቆች**: የተሟሉ ጐረቤቶችን የሚደግፍ የተለያዩ የመኖሪያ ቦታዎች እና የተደባለቁ ጥቅሞች ያላቸው ሰፈሮች

**የከተማ ማእከል**: ከተለያዩ ቅልቅል ጥቅሞች፣ የመኖሪያ ቤት፣ እና የስራ ስምሪት ጋር በክልላዊ የተሰየሙ ተጐራባቾች

**የከተማ መንደር**: በስፋት የመኖሪያ ቤት አይነቶች ካላቸው አካባቢዎች እና የሕዝብ ማመላለሻ፣ መገልገያዎች፣ እና ስራዎች ያሉባቸው

### አማራጭ 3: ሰፊ


በአሁኑ ጊዜ በግድግዳ የማይገነኙ ቤቶችን ብቻ በሚፈቅደው **የጐረቤት መኖሪያ (NR) ክልሎች** ውስጥ እንደ ባለሶስት ድርብ መኖሪያ፣ እና ባለአራት ድርብ መኖሪያ ያሉ ሰፊ ዝቅተኛ ደረጃ የመኖሪያ ቤቶች አማራጮች




**የተጐራባቾች የመኖሪያ አካባቢዎች**: ለመኖሪያ ቤቶች ምርጫዎች አዲስ ተለዋዋጭነትን በመላው የተጐራባቾች የመኖሪያ አካባቢዎች ውስጥ

### አማራጭ 4: ጠባብ መተላለፊያዎች/ ኮሪደሮች


ከተደጋጋሚ የሕዝብ መጓጓዣ እና ፓርኮች በ5 ደቂቃ የእግር መንገድ ውስጥ ተጨማሪ የመኖሪያ ቤት አማራጮች እና አገልግሎቶች




**ጠባብ መተላለፊያዎች/ ኮሪደሮች**: አዲስ ተለዋዋጭነት ያላቸው የመኖሪያ ቤት ምርጫዎች እና ሌሎች በሕዝብ መጓጓዣ እና ክፍት ቦታ አቅራቢያ ያሉ ጥቅሞች

### አማራጭ 5: የተደባለቁ

ተጨማሪ የመኖሪያ ቤት ምርጫዎችን እና የአገልግሎቶችን ተደራሽነት ለማቅረብ የስልቶች ድብልቅ



# የመኖሪያ ቤት


ጤናማ ማህበረሰቦች በአስተማማኝ እና በተረጋጋ መኖሪያ ቤት ላይ ይመረኮዛሉ። ቤት የአካል እና የአዕምሮ ጤናን፣ የገንዘብ መረጋጋትን፣ የትምህርት እና ኢኮኖሚያዊ እድሎችን እና የህይወት ጥራትን ይደግፋል።


የሲያትል የመኖሪያ ቤት ቀውስ ሰዎች ተመጣጣኝ የሆነ የቤት ዋጋ ለማግኘት እና ለእነሱ የሚሰራ መኖሪያ ውስጥ ለመቆየት አስቸጋሪ እያደረገው ነው። ለሲያትል ያለን ራዕይ ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው ቤተሰቦች እና ግለሰቦችን ጨምሮ ቤቶች ሁሉንም ዓይነት የመኖሪያ ቤት ምርጫዎች ያላት ሁሉን የምታቅፍ እና እንግዳ ተቀባይ የሆነች ከተማ ነው።

| | Detached house | Townhouse | Condo / co-op |
|---|---|---|---|
| Median sales price (2021) | $950,000 | $740,000 | $500,000 |
| Household income at which costs are affordable | 236% of AMI for a family of 3 | 184% of AMI for a family of 3 | 130% of AMI for a family of 2 |

AMI: የአካባቢ መካከለኛ ገቢ

Source: King County Department of Assessments





የመግለጫ ጽሑፍ: ቀይ መስመር (በስተቀኝ) ቤቶችን ለመግዛት እና ሀብትን ለማዳበር ብድር የማግኘት ደራሽነት የተነፈጉ የቀለም ማህበረሰቦች። የዘረኝነት ቃል ኪዳኖች በደርዘን በሚቆጠሩ የሲያትል ሰፈሮች ውስጥ (ግራ) የቀለም ሰዎች የንብረት ባለቤትነት እንዳይኖራቸው የሚገድቡ/የሚከለክሉ ህጋዊ ውሎች ነበሩ።

## የማይደረስበት መኖሪያ ቤት

በቅርብ ጊዜ የመኖሪያ ቤቶች ግንባታ ቢካሄድም፣ በገበያ ደረጃ እና በገቢ ገደብ በተመጣጣኝ ዋጋ ያለው የመኖሪያ ቤት እጥረት አሁንም እንደቀጠለ አለ። ይህም ለአብዛኞቹ የሲያትል አካባቢ ቤተሰቦች የቤት ባለቤትነትን የማይደረስበት ያደርገዋል እና የኪራይ ቤቶችን የበለጠ ውድ ያደርገዋል። በሀብት፣ በቤት ባለቤትነት፣ የመኖሪያ ቤት የዋጋ ሸክም፣ እና የቤት አጥነት ልዩነቶች በመኖሪያ ቤቶች ስርዓታችን ውስጥ ያለውን የእኩልነት ኢፍትሃዊነት ያሳያል።

**የእኛ የመኖሪያ ቤቶች ገጽታ ሁለቱንም ማለት የገበያ ኃይሎች እና የአድሎአዊ ተሞክሮዎችን ታሪክ ያንፀባርቃል።** ባለፈው ወቅት ውስጥ፣ ዘረኛ የመኖሪያ ቤት ፖሊሲዎች እና ተግባራት ለቀለም ሰዎች የቤት ባለቤትነትን ሙብት በግልፅ የነፈጉ እና የት መኖር እንደሚችሉ የሚገድቡ ነበሩ።

### Homeownership in Seattle by race of householder




Source: American Community Survey, 2016-2020

## መኖሪያ ቤት በአጠቃላዩ እቅድ ውስጥ

+ ዕቅዱ ለሁለቱም የገበያ ደረጃ ላላቸው መኖሪያ ቤቶች እና በተመጣጣኝ ዋጋ ለተመደቡ የመኖሪያ ቤቶች አንድ የወደፊት ራዕይን ይመሰርታል። እድልን ለማስፋት፣ የወደፊቱን እድገት ለማስተናገድ፣ በዋጋ ላይ የሚደረገውን ጫና ለመቀነስ፣ እና ያለፉትን የምርት እጥረት ጉዳይ ለመነጋገር **የመኖሪያ ቤት አቅርቦትን ማሳደግ።**
+ የአሁኑን እና የወደፊት ነዋሪዎችን ፍላጎቶች በተሻለ ሁኔታ የሚያሟሉ **በበለጠ የተለያዩ የመኖሪያ ቤቶች ዓይነቶችን ማበረታታት።**
+ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ቤተሰቦችን ፍላጎቶች ለማሟላት፣ **በገቢ የተገደበ ተመጣጣኝ የኪራይ ዋጋ እና የሽያጭ መኖሪያ ቤቶችን ማልማት እና ለትውልድ ማቆየት።**
+ **መፈናቀልን መከላከል እና መገለልን ወደፊት አውጥቶ መነጋገር።**

# የፀረ-መፈናቀል ስልቶች

## መፈናቀል ምንድን ነው?

መፈናቀል ከራሳቸው ቁጥጥር ውጪ በሆኑ ሃይሎች ሳቢያ ነዋሪዎችን፣ የንግድ ድርጅቶችን፣ እና ተቋማትን ያለፍላጎታቸው ከቦታቸው ማፈናቀል ነው። ዋነኛው መንስኤው የመኖሪያ ቤቶች እና የንግድ ቦታዎች እጥረት እና እየጨመረ የሚሄደው የቤቶች ዋጋ ነው። እንዲሁም ሰዎች ደግሞ ከቤት በማስወጣት፣ በመልሶ ግንባታ፣ ወይም በገቢ ገደብ የተከለከሉ ቤቶች ላይ ቃል ኪዳኖች ወቅታቸው በማብቃታቸው ተፈናቅለዋል።


## ለመፈናቀል ግፊቶች ምላሽ መስጠት

እቅዱ ወሳኝ የሆነ ዋጋን ወደ ላይ ከፍ የሚያደርገውን እጥረት ፊት ለፊት በማቅረብ፣ የመኖሪያ ቤት አቅርቦትን እና ምርጫን እንድንጨምር ይረዳናል። ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ቤተሰቦች፣ የቀለም ሰዎችን፣ የBIPOC ንግዶች እና ተቋማትን፣ እና ሌሎች በመፈናቀል አደጋ ላይ ያሉ ሰዎች ላይ የሚደርሰውን ጫና በመቀነስ ተጨማሪ መኖሪያ ቤቶችን የት ማበረታታት እንዳለብን ለመለየት የመፈናቀል ስጋት አመልካችን (Displacement Risk Index) እየተጠቀምን ነው።

## የፀረ-መፈናቀል መሳሪያዎች ሊሆኑ የሚችሉ የሚከተሉትን ያካትታሉ፥

- በመላ ከተማው ሁሉ ለመኖሪያ ቤቶች ተመጣጣኝ ዋጋ አዲስ መስፈርቶች ወይም ማበረታቻዎች
- የተመጣጣኝ ዋጋ የመኖሪያ ቤቶችን እና ፍትሃዊ እኩልነት ያለው የልማት ፕሮጀክቶችን የበለጠ ተግባራዊ ለማድረግ እና የህዝብ መዋዕለ ንዋዮችን እጅጉን ለማሳደግ ለውጦችን ማድረግ
- የማህበረሰብ ድርጅቶች ንብረት መግዛት እንዲችሉ የገንዘብ ድጋፍ መስጠት
- እንደ የማዘዋወር እርዳታ ያሉ፣ ይበልጥ ጠንካራ የተከራይ ጥበቃዎች መስጠት
- አሁን ላሉ ነባር ንግዶች እና ተቋማት በቦታቸው እንዲቆዩ ለመርዳት ድጋፎች

### Preliminary Displacement Risk Index




The Displacement Risk Index is based on neighborhood characteristics like the presence of vulnerable populations and amenities that increase real estate demand. This analysis helps us evaluate likely outcomes of different alternatives and potential strategies to address the displacement pressures community members are experiencing today.



በ2021፣ የኢትዮጵያ መንደር ግንባታ የመሬት መመረቂያ

## አንድ ሲያትል (One Seattle) አጠቃላይ እቅድ

# የመኖሪያ ቤት ዓይነቶች

የመኖሪያ ቤት ዓይነቶች በመኖሪያ ቤቶቹ ቁጥር፣ እንዴት እንደተደራጁ፣ በባለቤትነት ወይም የተከራዩ በመሆን ይለያያሉ። ይህ ሰሌዳ በሦስት ምድቦች ውስጥ የተለያዩ የቤት ዓይነቶች ምሳሌዎችን ያሳያል ።

## የተራራቁ መኖሪያ ቤቶች ከሌላ ከማንኛውም ቤት ጋር ግድግዳዎችን የማይጋሩ የራሳቸው መዋቅር ውስጥ የሆኑ ናቸው





**በትንሽ ቦታ ላይ የተነጠለ የመኖሪያ ቤት**
ነባር የተጠበቀ መኖሪያ ቤት ከሁለት አዳዲስ ቤቶች ከኋላ ታክለው የተጨመሩ (በግራ) እና ሶስት ቤቶች በአንድ ቦታ ላይ (በስተቀኝ)




**የተነጠለ ተጨማሪ የመኖሪያ ቤት (DADU)**
አብዛኛውን ጊዜ ከዋናው ቤት ጀርባ የሚሆን፣ አንድ በመኖሪያ ቦታ ላይ የታከለ ሁለተኛ ክፍል/ የመኖሪያ ቤት



**የመኖሪያ ቤት ጎጆ**
የጋራ ክፍት ቦታ ዙሪያ የተደራጁ/ የተደረደሩ ከ2-3 ፎቅ ያላቸው የተናጠል መኖሪያ ቤቶች


## የተያያዙ ቤቶች ግድግዳዎችን ከሌሎች ቤቶች ጋር ይጋራሉ፣ እያንዳንዱ ክፍል/ መኖሪያ በቀጥታ በባለቤትነት የተያዘ






**ለት ድርብ መኖሪያ ቤቶች እና ሶስት ድርብ መኖሪያ ቤቶች (ጎን ለጎን)**
አንዱ ከሌላው ጋር ግድግዳዎችን የሚጋሩ ሁለት ወይም ሶስት ክፍሎች/ የመኖሪያ ቤቶች






**የከተማ ቤት እና ጐን ለጐን ያሉ መደዳ ቤቶች**
ሙሉ በሙሉ በባለቤትነት ሊያዙ የሚችሉ አንድ ግድግዳ ከሌላ መኖሪያ ቤት ጋር የሚጋሩ የመኖሪያ ቤት





**በአንድ ግቢ ውስጥ ያሉ አፓርታማዎች**
በአንድ የጋራ ክፍት ቦታ ዙሪያ የተደራጁ/የተደረደሩ ከ2-3 ፎቅ ያላቸው የተያያዙ መኖሪያ ቤቶች

## የተደራረቡ መኖሪያ ቤቶች በአቀባዊ የተደረደሩ በርካታ ክፍሎችን የሚያካትቱ መኖሪያ ቤቶች


**አራት ማዕዘን የኩብ ቅርጽ ያለው መኖሪያ ቤ ት**
አንድ ባህላዊ ቅፅ ከሚከተሉት ጋር በአንድ ወለል ውስጥ ሁለት የመኖሪያ ክፍሎች ብዙውን ጊዜ ከትልቅ ቤት ጋር የሚመሳሰል አንድ ቅርጽ



**ስድስት የተለያዩ መኖሪያ ቤቶች የያዘ ህንጻ**
ንድ ባለ ሶስት ፎቅ መዋቅር በአንድ ወለል ሁለት ቤቶች ያሉት





**8-የተለያዩ መኖሪያ ቤቶች የያዘ ህንጻ**
አንድ ባለ አራት ፎቅ መዋቅር በአንድ ወለል ሁለት መኖሪያ ቤቶች ያሉት



**ከ5-8 ፎቅ ያላቸው አፓርታማዎች እና የጋራ መኖሪያ ቤቶች**
እንደ አፓርታማ ሊከራዩ የሚችሉ ወይም በባለቤትነት የተያዙ ብዙ ቤቶች በአንድ ከ5-12 ፎቅ ያላቸው ሕንፃዎች እንደ ኮንዶሚኒየም ክፍሎች





**ባለ ብዙ ፎቅ አፓርታማዎች እና የጋራ መኖሪያ ቤቶች**
ከ12 ፎቅ በላይ ያላቸው ህንጻዎች በአንድ ፎቅ ብዙ መኖሪያ ቤቶች ያሉት እንደ አፓርታማ የሚከራዩ ወይም እንደ ኮንዶሚንየም በባለቤትነት የተያዙ

## የOne Seattle አጠቃላይ እቅድ

# ፓርኮችና ክፍት ቦታ

ፓርኮችና ክፍት ቦታዎች ለማህበረሰቦቻችንና አካባቢያችን ጤናማነትና ደህንነት ወሳኝ ቦታዎች ናቸው። የሲያትል ከቤት ውጭ የማህበረሰብ መሰብሰቢያ ቦታ ኔትወርክ ብዙ የተለያዩ አይነት ቦታዎችን እና መገናኛዎችን ማለትም፡ ፓርኮችን፣ የእግር መንገዶችን፣ P-ተለጣፊ የአትክልት ቦታዎችን፣ የመኖሪያ መንደር አረንጓዴ መንገዶችን፣ የባህር ዳርቻ የመንገድ መጨረሻዎችን እና ብዙ ሌሎችንም ያጠቃልላል።  ይህ ኔትወርክ የምንዝናናበት፣ የምንንቀሳቀስበት፣ የምንጫወትበት፣ ከተፈጥሮ ጋር የምነምገናኝበት፣ በትዕይንቶችና የባህል ዝግጅቶች የምንዝናናበት፣ ከጎረቤቶቻችን ጋር የምንሰባሰብበት እና ከጓደኞቻችንና ቤተሰባችን ጋር የምነምገናኝበት እድሎች ያቀርብልናል።

ሲያትል ውስጥ የሚገኙ ከ1,000 የሚበልጡ የተለያዩ የማህበረሰብ መሰብሰቢያ ቦታዎች በአገሪቱ ውስጥ እጅግ ተመራጩ የማህበረሰብ መሰብሰቢያ ቦታ ስርአቶች ውስጥ አንዱን ይፈጥራሉ። ብሔራዊ ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት የሆነው የማህበረሰብ መሬት ባለአደራ የሲያትል ሲስተምን በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ከሚገኙ ከ10 ከፍተኛ ሲስተሞች መካከል አንዱ አድርጎ የመደበው ቢሆንም አሁንም ለመሻሻል መስራት የምንችለው ስራ አለ።

ቀደም ሲል የተደረጉ የኢንቨስትመንት ውሳኔዎች በአካባቢና የአረንጓዴ ቦታ መድረስ ላይ ይደረጉ የነበሩ ከፍተኛ የዘር ልዩነቶችን የሚያስቀጥሉ ነበሩ። ወደፊት የሚካሄዱ የአረንጓዴ ኢንቨስትመንቶች የBIPOC ማህበረሰቦችን ባሉበት ቦታ እድገት እንዲያመጡ የሚያስችሉ ስራዎች፣ የኢኮኖሚ ዕድሎች ከመፍጠርና ተመጣጣኝ ዋጋ ያላቸው መኖሪያ ቤቶች ከማቅረብ ጎን ለጎን እነዚህን ልዩነቶች በመፍታት ላይ ማተኮር አለባቸው።



**ለማህበረሰብ መሰብሰቢያ ቦታ እኩል ተደራሽ መሆን**



**የአካባቢ ፍትሕና የአካባቢ ጤና**



**ባህል፣ ኪነ ጥበቦችና ማህበረሰብ**

**የመቋቋም አቅምና የአየር ንብረት ለውጥ ማቅለያ**

## ዋና ዋና ጉዳዮች

በዚህ አጠቃላይ የእቅድ ማሻሻያ ስር የሲያትልን የህዝብ መሰብሰቢያ ቦታ ኔትወርክ የሚያስፋፉ፣ የሚያገናኙ፣ የሚያሻሽሉና የሚያስቀጥሉ ስትራቴጂዎችን እናጠናለን። በምንሰራው ስራ ላይ ሁሉ በማደግ ላይ የሚገኘውን ከተማችንን የሁሉንም ማህበረሰቦች ጤናና ደህንነት ለመደገፍ የዘር እኩልነትን ማዕከል አድርገን እንሰራለን። የአየር ንብረት ለውጥ ባጋጠመበት ሁኔታ የማህበረሰብ መሰብሰቢያ ቦታ እንዴት መቋቋሚያ በማቅረብ እንደሚረዳ እናጠናለን። በተጨማሪም በመፈናቀል ተጋላጭ ለሆኑ የመኖሪያ መንደሮች አረንጓዴ ማሻሻያዎችን የማህበረሰቡን መረጋጋት በሚደግፉበት መልኩ ማቅረብ የምንችልባቸውን ዘዴዎች እናጠናለን።

## አሁን ምን እየሰራን እንደሆነ

- ወቅታዊ የሲያትል የፓርኮችና የመዝናኛ (SPR) ፕሮጀክቶችና ኢኒሺየቲቮች
- የSPR ስትራቴጂያዊ እቅድ ትግበራ
- የሲያትል ከቤት ውጭ ከተማ አቀፍ ፕሮግራም
- የሲያትል የትራንስፖርት መምሪያ የህዝብ መሰብሰቢያ ቦታ አስተዳደር ፕሮግራም

## እስኪ ሥለ ወደፊት እንነጋገር

የህዝብ መሰብሰቢያ ቦታዎቻችንን እንዴት የበለጠ ጋባዥና ጠቀሜታ ላይ የሚውሉ ማድረግ እንችላለን?

የፓርኮችና ክፍት ቦታዎች መገናኘትን ማሻሻል የምንችልባቸው ዘዴዎች ምንድን ናቸው?

የህዝብ መሰብሰቢያ ቦታዎች እንዴት የአካባቢና የሰዎችን ጤና በሚደግፍ መልኩ ሊሻሻሉ ይችላሉ?

የማህበረሰብ መሰብሰቢያ ቦታ ሲስተማችን የአየር ንብረት ለውጥ ባጋጠመበት ሁኔታ እንዴት የማህበረሰብ መቋቋሚያ አቅም ሊያቀርብ ይችላል?

የማህበረሰብ መሰብሰቢያ ቦታዎችን ተጨማሪ ነዋሪዎችን እንዲያስተናግዱ ማድረግ የሚቻልባቸው ዘዴዎች ምንድን ናቸው?

ሰዎችን ከቤት ውጭ ተጨማሪ ጊዜ እንዲያሳልፉ የሚጋብዙ ተግባሮች ወይም ዝግጅቶች ምንድን ናቸው?

አስተያየቶችዎን ለሚከተለው ይላኩ:
**oneseattlecompplan@seattle.gov**

ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት የሚከተለውን ይጎብኙ:
**seattle.gov/opcd/one-seattle-plan**

ይህን ሰነድ በተለዋጭ ፎርማት ወይም ቋንቋ ለማግኘት oneseattlecompplan@seattle.gov ን ያነጋግሩ፤ ለዝግጅት ወይም ስብሰባ የአካል ጉዳተኞች አገልግሎት በመጀመሪያ ዕድልዎ ለመጠየቅ oneseattlecompplan@seattle.gov ን ያነጋግሩ።

Seattle

## የOne Seattle አጠቃላይ እቅድ

# የአየር ንብረት ለውጥ

አሁን የአየር ንብረት ለውጥ እያጋጠመ ከመሆኑም ባለፈ ተጽእኖዎቹ ማህበረሰባችንን እየጎዱ ነው። እጅግ በጣም ከሚያቃጥሉ የሙቀት ሞገዶች እና አየራችንን የሚያፍኑ የዱር ሰደድ እሳቶች አንስቶ እስከ የባህሮች ከፍታ መጨመርና መንገዶቻችን አጥበው የሚወስዱ ከባድ የጎርፍ መጥለቅለቆች ድረስ ሲያትል የአየር ንብረት ለውጥ ተፅእኖዎች በትር እያረፈባት ነው። ልክ እንደ አብዛኞቹ ከተሞች ሁሉ ሲያትል እነዚህን ጎጂ ተጽእኖዎች ለመቆጣጠር እየሰራ ነው። በተመሳሳይ ጊዜ ከሁለቱ ትላልቅ ምንጮቻችን ማለትም፡ ትራንስፖርትና ህንጻዎች የሚወጡ ለአየር ንብረት ለውጥ አስተዋጽኦ የሚያደርጉ የካርቦን ልቀቶችን ለመቀነስ አሁን እርምጃ መውሰድ አለብን።

የአየር ንብረት ግቦቻችንን ማሳካት ማለት በተጨማሪም በታሪክ ሂደት ውስጥ በኢኮኖሚ፣ የዘርና አካባቢ ኢፍትሀዊነቶች እጅግ በተጎዱ ማህበረሰቦች ውስጥ ለሚካሄዱ ኢንቨስትመንቶች ቅድሚያ በመስጠት ስራዎች መፍጠሪያና ወደ ታዳሽ ሀይል ተመጣጣኝ ሽግግር ማድረጊያ ዕድል መፍጠር ነው።

## የሲያትል ወደ ከባቢ አየር የግሪንሃውስ ጋዝ ልቀቶች እያደጉ መጥተዋል።

ቆሻሻ

ህንጻዎች

ኢንዱስትሪ

ትራንስፖርት




## በአጠቃላይ የእቅድ ማሻሻያ ውስጥ ለአየር ንብረት ለውጥ የሚሰጠው ትኩረት

አጠቃላይ ዕቅዱ ከህንጻዎችና ትራንስፖርት የሚወጡ ልቀቶችን መቀነስ፣ እና ከተማችንን የበለጠ የአየር ንብረት ለውጥ ተጽእኖዎችን መቋቋም የሚችል ማድረግ ላይ ያተኮሩ አዲስ የአየር ንብረት ለውጥ ፖሊሲዎችን ያካትታል። የረጅም ጊዜ ፖሊሲዎች ሲያትልን በ2050 ዓ.ም ከካርቦን ነጻ ወደመሆን ያስጠጉታል እንዲሁም የባህር ከፍታዎች መጨመር፣ የሙቀት ሞገዶች፣ የጎርፍ አደጋና በጣም አስቸጋሪ አውሎ ንፋሶች ቢኖሩም እንኳ ማደግ የሚችል ከተማ ለመገንባት ያግዛሉ። ሲያትል አገራዊ፣ ክልላዊና ግዛት አቀፍ ግቦችን ለማሳካት ከአጋሮቻችን ጋር ለመስራት ቁርጠኛ ነው።

## ዋና ዋና ጉዳዮች



ልቀቶችን መቀነስ



አረንጓዴ ስራዎች



የአየር ንብረትን መላመድና መቋቋ

## አሁን ምን እየሰራን እንደሆነ

- [ወደ ከባቢ አየር የሚደረጉ የግሪንሃውስ ጋዝ ልቀቶችን መቆጣጠር]
- [ትራንስፖርትን ወደ ንጹህ የሀይል ምንጮ/ኢነርጂ መቀየር]
- [የበለጠ አረንጓዴ ህንጻዎችን መገንባት]
- [የከተማ አገልግሎት መስጫዎችን መላመድ]
- [ስለ ፍትሀዊና ተመጣጣኝ/ዕኩል ሽግር ማቀድ]
- [የፊት መስመር ማህበረሰቦችን የአየር ንብረት ለውጥ ተጽእኖዎች ተጋላጭነት በጣም ዝቅተኛ ማድረግ]
- [በአየር ንብረት ለውጥ ለሚባባሱ የተፈጥሮ አደጋዎች ተጋላጭ ቦታዎችን ካርታ ማስመር/መከለል]

## እስኪ ሥለ ወደፊት እንነጋገር

የአየር ንብረት ለውጥን በተመለከተ
እጅግ የሚሰጋዎት ነገር ምንድን ነው?

ከተሽከርካሪዎች እና ህንጻዎች የሚወጡ ወደ የግሪንሃውስ ጋዝ ከባቢ
አየር ልቀቶችን ለመቀነስ በተጨማሪ ምን ማድረግ እንችላለን?

ወደ ዜሮ ካርቦን ልቀቶች በመሸጋገር ረገድ ስራዎችና
ዕድሎችን ለመፈጠር በተጨማሪ ምን ማድረግ እንችላለን?

ለአየር ንብረት ለውጥ ተጽእኖዎች (የባህር ከፍታ
መጨመር፣ ጎርፍ፣ እጅግ አስቸጋሪ ሙቀት፣ ወዘተ) እጅግ
ተጋላጭ የሆኑ ቦታዎችና ሰዎችን ደህንነት ለመጠበቅ
በተጨማሪ ምን ማድረግ እንችላለን?



አስተያየቶችዎን ለሚከተለው ይላኩ:
**oneseattlecompplan@seattle.gov**

ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት የሚከተለውን ይጎብኙ:
**seattle.gov/opcd/one-seattle-plan**

ይህን ሰነድ በተለዋጭ ፎርማት ወይም ቋንቋ ለማግኘት oneseattlecompplan@seattle.gov ን ያነጋግሩ፤ ለዝግጅት ወይም ስብሰባ የአካል ጉዳተኞች አገልግሎት በመጀመሪያ ዕድልዎ ለመጠየቅ oneseattlecompplan@seattle.gov ን ያነጋግሩ።

# ፍትሃዊ እኩልነትን ማዕከል ማድረግ

## ያለፉትን ጉዳቶች አውጥቶ መፍታት

የሲያትል የዕቅድ ታሪክ በዘር፣ በጎሳ፣ እና በመደብ መስመሮች አግልሎ የሰዎችን መከፋፈልን እና አድልዎችን በፈጠሩ እና እንዲቀጥል ባደረጉ በዘረኛ የመሬት አጠቃቀም እና የመኖሪያ ቤት ፖሊሲዎች እና ልምዶች በግልጽ ይታያል።



ይህ የማግለል ስርዓተ-ጥለት የጀመረው በሲያትል ውስጥ ማን መድረስ እና መኖር እንደሚችል ከሚገድቡ ህጎች ጋር የታጠቁ ነጭ ሰፋሪዎች ከመጡ በኋላ ነበር። ይህ አሰራር እስከ 20ኛው ክፍለ ዘመን ድረስ የቀለም ሰዎች የቤት ብድሮችን መድረስ እንዳይችሉ እና እንዲሁም በዘረኝነት የተገደቡ ቃል ኪዳኖችን የቀይ መስመር ሽፋን ሰጥተውት ቀጥለዋል።

ዛሬም ድረስ የዚህ ታሪክ ተፅእኖዎች በግትር ቋሚ የመለያየት አድልዎ እና ልዩነቶች እየታየ ይገኛል። እነዚህ ውጤቶች በበርካታ ሰፈሮች ውስጥ ዝቅተኛ ዋጋ ያላቸው የመኖሪያ ቤቶች ምርጫዎች መኖራቸውን የሚገድቡ አሁን ባለው የመሬት አጠቃቀም ደንቦች የተጠናከሩ ናቸው።

የሲያትል አጠቃላይ እቅድ የበለጠ የዘር ፍትሃዊ እኩልነት የወደፊት ሁኔታን ለመቅረጽ ያለን ዕድላችን ነው።



## የዘር እኩልነትን ወደፊት ማስኬድ


እቅዱ የዘር ፍትሃዊነትን እንዴት ወደፊት እንድሚያስኬድ ለማረጋገጥ፣ እንደ የሲያትል የዘር እና የማህበራዊ ፍትህ ተነሳሽነት አካል የምንጠቀመውን የኛን የዘር እኩልነት መሣሪያ ስብስብ እየተጠቀምን ነው። እንደ አንድ የመጀመሪያ እርምጃ፣ በአንድ የሲያትል እቅድ ውስጥ ልናሳካቸው የምንሻቸውን ረቂቅ የዘር እኩልነት ውጤቶችን ለይተናል። እቅዱን እያጠናቀቅን ስንሄድ ከተማዋን ተጠያቂ ለማድረግ የማህበረሰብ አባላት ደግሞ እነዚህን የዘር እኩልነት ውጤቶች መጠቀም አለባቸው።

አሁን በእነዚህ ረቂቅ የዘር እኩልነት ውጤቶች ላይ የማህበረሰብ አስተያየት እየጠየቅን ነው። እቅዱን ለመምራት ምን የዘር እኩልነት ውጤቶች ልንጠቀምባቸው ይገባል? በተለይ ከቀለም ሰዎች እና ማህበረሰብን መሰረት ካደረጉ ድርጅቶች የተገኘ ግብአት በጣም አስፈላጊ ነው።

የበለጠ ይወቁ እና የእኛን
የዳሰሳ ጥናት ይውሰዱ።

ስለ የሲያትል አድሎአዊ እቅድ አዘገጃጀት እና የመሬት አጠቃቀም ተሞክሮዎች ታሪክ እና ፍትሃዊ እኩልነትን በአንድ ሲያትል አጠቃላይ እቅድ (One Seattle Comprehensive Plan) ላይ እንዴት እንዳማከልን የበለጠ ይወቁ።

Watch the video



Seattle

## የOne Seattle አጠቃላይ እቅድ

# መኖሪያ ቤት

ጤናማ ማህበረሰቦች በሁሉም አስተማማኝና የተረጋጋ መኖሪያ ቤት ባላቸው ቤተሰቦች ላይ የተመሰረቱ ናቸው። መኖሪያ ቤት ለብዙ የደህንነት ጉዳዮች ወሳኝ ናቸው፤ ለምሳሌ፡ ለአካልና የአእምሮ ጤና፣ የገንዘብ መረጋጋት፣ የትምህርትና ኢኮኖሚያዊ ዕድል፣ እና ጥራቱን የጠበቀ አኗኗር። ከሲያትል እያደገ መሄድ ጋር ተያይዞ አካታችና ጋባዥ/ ተቀባይ ከተማ የመፍጠር ራዕያችን ተጨማሪ ሁሉንም አይነት መኖሪያ ቤቶች መገንባትን እና ተመጣጣኝ ዋጋ ያላቸው መኖሪያ ቤቶች ላይ ኢንቨስት ማድረግን ያጠቃልላሉ።

ያም ሆኖ ግን ሲያትል ውስጥ የመኖሪያ ቤት ተደራሽት ዕኩል/ ተመጣጣኝ አይደለም። የመኖሪያ ቤት ምህዳራችን የገበያ ሀይሎች መርና የማግለል ታሪክ የያዙ አሰራሮች መኖርን ያሳያል። ባለፉት ዘመናት የተለየ ቀለም ያላቸው ሰዎችን የቤት ባለቤት እንዳይሆኑ ለማድረግና የሚኖሩበትን ቦታ ለመገደብ እንደ ቀይ መስመር ማስመርና በዘር የሚገድቡ ስምምነቶች የመሳሰሉ ዘረኛ ፖሊሲዎችና አሰራሮች ጥቅም ላይ ይውሉ ነበር።

በአሁኑ ወቅት በውሱን መኖሪያ ቤቶች ላይ የሚደረገው ውድድር የመኖሪያ ቤት ዋጋዎችን ከፍ አድርጓቸዋል። በክልላችን ውስጥ የኪራይ መኖሪያ ቤት ዋጋ ለብዙዎች ውድ/ከአቅም በላይ ነው። ከፍተኛ የመኖሪያ ቤት ወጪዎች ሰዎችን ከመኖሪያቸው ማፈናቀላቸውን የቀጠሉ ሲሆን አንዳንዶች በዚህ ምክንያት የመኖሪያ ቤት አልባ ሆነዋል። እንዲሁም የቤተሰቦች የመጀመሪያ ሀብት ማፍሪያና ማስተላለፊያ ዘዴ የሆነው — የቤት ባለቤትነት — ለአብዛኞቹ የራሳቸው መኖሪያ ቤት የሌላቸው ቤተሰቦች ለመድረስ በጣም ሩቅ ሆኗል።

ባለፉት 10 ዓመታት ውስጥ ሲያትል ውስጥ ከ70,000 በላይ አዲስ መኖሪያ ቤቶች የተገነቡ ቢሆንም አሁንም ግን እያደገ የሚሄደውን የመኖሪያ ቤት ፍላጎት ለማሟላት በቂ መኖሪያ ቤቶችን አልገነባንም። አብዛኞቹ የሲያትል ቦታዎች እንደ አፓርታማዎች የመሳሰሉ ተመጣጣኝ ዋጋ ያላቸው መኖሪያ ቤቶችን አያቀርቡም። እንዲሁም የማዘጋጃ ቤት የሆኑ መኖሪያ ቤቶችና ትናንሽ ለየብቻ የሚሰሩ መኖሪያ ቤቶችን ጨምሮ ለአብዛኞቹ ልጆች ያሏቸው ቤተሰቦች በተመጣጣኝ ዋጋ የሚቀርቡ መኖሪያ ቤቶችን በበቂ ሁኔታ እየሰራን አይደለንም። ከ2012 እስከ 2019 ዓ.ም መካከለኛ ገቢ ያላቸው የሲያትል ቤተሰቦች የዋጋ ግሽበት ማስተካከያ በኋላ 46% የመኖሪያ ቤት ወጪ ጭማሪ አጋጥሟቸዋል። በአሁኑ ወቅት ለብቻቸው የሚሰሩ መኖሪያ ቤቶች አማካኝ የሽያጭ ዋጋ ከ$1 ሚሊዮን በላይ ነው። የወጪዎች እየጨመረ መሄድ ማህበረሰቦችን የሚወዷቸውን ሰዎች ጥለው ወደ ሌሎች ቦታዎች እንዲሄዱ ያስገድዷዋል።

በቁጥር ያልተመጣጠኑ የተለየ ቀለም ያላቸው ዝቅተኛ ገቢ የሚያገኙ ቤተሰቦች ሲያትል ውስጥ የሚያገኙት እጅግ ጥቂት የተመጣጣኝ ዋጋ አማራጮችን ነው። ባለፉት አምስት አመታት ውስጥ የሲያትል ከተማ ከ6,000 በላይ ለሆኑ በተመጣጣኝ ዋጋ የሚቀርቡ የኪራይና የሽያጭ መኖሪያ ቤቶች ልማትና ማስቀጠል ድጋፍ አድርጓል። የተጨማሪ 7,500 በገቢ ልክ የተገደቡ መኖሪያ ቤቶች ግንባታ በሂደት ላይ ነው። ታሪካዊ የከተማ ኢንቨስትመንቶች ቢደረጉም እንኳ አሁንም የሲያትልን የመኖሪያ ቤት ውድነት ቀውሶች ለመፍታት የሚያስፈልጉት መኖሪያ ቤቶች ክፍተት አለብን።





# በአጠቃላይ የእቅድ ማሻሻያው ስር ለመኖሪያ ቤት የተሰጠው ትኩረት

የመኖሪያ ቤትን የተመለከተው ክፍል የወደፊት የገበያ ተመንን መሰረት ያደረጉ መኖሪያ ቤቶችና ቁጥጥር የሚደረግባቸው ተመጣጣኝ ዋጋ ያላቸው መኖሪያ ቤቶች ራዕይ አለው። መኖሪያ ቤት የዕድገት ስትራቴጂ እና የመሬት አጠቃቀም ወሳኝ ክፍል ተደርጎ የተወሰደ ሲሆን የእድገት ስትራቴጂው የት የተለያዩ አዲስ የመኖሪያ ቤት አይነቶች እንዲሰሩ እንደምንፈቅድና እንደምናበረታታ እንዲሁም የመሬት አጠቃቀም እንዴት ደንቦች አዲስ ልማትን ቅርጽ እንደሚያስይዙ ይገልጻሉ።

## ዋና ዋና ጉዳዮች

ከፍተኛ የመኖሪያ ቤት እጥረት
የኪራይ ዋጋዎችና የቤት ሽያጭ ዋጋዎች መጨመር
ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው ቤተሰቦች የመኖሪያ ቤት ማግኛ ምንጮች
ትናንሽና አነስተኛ ዋጋ ያላቸው ቤቶች መስራት
በመኖሪያ ቤት ተደራሽትና የቤት ባለቤትነት ላይ የሚደረጉ የዘር ልዩነቶች
መፈናቀል
የመኖሪያ ቤት አልባነት ስጋቶች እያደጉ መምጣት

## አሁን ምን እየሰራን እንደሆነ

- በገቢ ልክ የተገደቡ በተመጣጣኝ ዋጋ የሚቀርቡ የኪራይና የሽያጭ መኖሪያ ቤቶች ልማትና ማስቀጠል
- የመኖሪያ ቤት ገበያን
  በመኖሪያ ቤት ምርጫዎች ኢኒሺየቲቫችን አማካኝነት በመኖሪያ ቤት ጉዳዮች ላይ ማሳተፍ
- ማህበረሰቡን
  በመኖሪያ ቤት ምርጫዎች ኢኒሺየቲቫችን አማካኝነት በመኖሪያ ቤት ጉዳዮች ላይ ማሳተፍ
- ከፍተኛ የመፈናቀል ስጋት ያለባቸውን ማህበረሰቦች ለይቶ ማወቅ

## እስኪ ሥለ ወደፊት እንነጋገር

በመኖሪያ መንደርዎ ምን አይነት መኖሪያ ቤቶች በተጨማሪ ተሰርተው ማየት ይፈልጋሉ?

ተጨማሪ መኖሪያ ቤቶች በየትኞቹ የሲያትል ክፍሎች መሰራት አለባቸው ብለው ያስባሉ?

አዲስ የሚሰሩ መኖሪያ ቤቶች ምን አይነት ጥራት እንዲኖራቸው ይፈልጋሉ?

የሲያትል ነዋሪዎችን ከመኖሪያ ቤቶቻቸው መፈናቀል እንዴት ልንቀንስው እንችላለን?

ከተማው የመኖሪያ ቤት አቅርቦትን፣ የዋጋ ተመጣጣኝነትን እና የተለያዩ አይነት የመሆን አማራጮችን ለማሳደግ ምን ስትራቴጂዎችን መከተል አለበት?

አስተያየቶችዎን ለሚከተለው ይላኩ:
**oneseattlecompplan@seattle.gov**

ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት የሚከተለውን ይጎብኙ:
**seattle.gov/opcd/one-seattle-plan**

ይህን ሰነድ በተለዋጭ ፎርማት ወይም ቋንቋ ለማግኘት oneseattlecompplan@seattle.gov ን ያነጋግሩ፤ ለዝግጅት ወይም ስብሰባ የአካል ጉዳተኞች አገልግሎት በመጀመሪያ ዕድልዎ ለመጠየቅ oneseattlecompplan@seattle.gov ን ያነጋግሩ።

Seattle

## የOne Seattle አጠቃላይ እቅድ

# የዕድገት ስትራቴጂ

የአጠቃላይ ዕቅዱ የእድገት ስትራቴጂ የከተማውን በቀጣይ 20 ዓመታት ውስጥ የሚካሄደውን ግንባታ የሚጠበቀው የህዝብና የስራ ዕድገት ፍላጎቶች የሚያሟላ የማድረግ እና የከተማውን ግቦች የሚሳካ የማድረግ ራዕይ ነው።

## በአጠቃላይ ዕቅዱ ውስጥ ለእድገት ስትራቴጂ የተሰጠው ትኩረት

የእድገት ስትራቴጂው ክፍል የመኖሪያ፣ የንግድና የኢንዱስትሪ ልማት የት መካሄድ እንዳለበት እና አዲስ ልማት እንዴት ከከተማው ኢንቨስትመንቶች ጋር መጣጣም እንዳለበት ይገልጻል። ይህ ክፍል በከተማው ውስጥ በሙሉ የሚሰሩ አዲስ መኖሪያ ቤቶች (አፓርታማዎች፣ የማዘጋጃ ቤት መኖሪያ ቤቶች፣ ለብቻቸው የሚሰሩ መኖሪያ ቤቶች) አይነቶችን እና የሚሰሩበትን ቦታ ቅርጽ ያስይዛል። ክፍሉ በተጨማሪም ከተማው እያደጉ ለሚመጡ መኖሪያ መንደሮች ድጋፍ ለማድረግ የት እንደ የትራንዚት አገልግሎት የመሳሰሉ አዳዲስ ኢንቨስትመንቶችን እንደሚገነባ ይመራል።

በዚህ ክፍል ስር የተገለጸው ራዕይ የወደፊት የከተማውን የዞን አከላለል ለውጦችና የልማት ደንቦች ቅርጽ የሚያስይዝ ሲሆን የልማት ደንቦቹ በተለያዩ ቦታዎች የሚፈቀዱ ህንጻዎች አይነትና ብዛት ይገልጻል። ይህ የወደፊት ልማት ንድፍ በተጨማሪም ከተማው እንዴትና የት የማህበረሰብ መገልገያዎችና የጸረ-መፈናቀል እፈርምጃዎች ላይ ኢንቨስት እንደሚያደርግ መረጃ ይሰጣል።

## የወቅታዊ ዕድገት ስትራቴጂ

የእቅዱ የወቅታዊ ዕድገት ስትራቴጂ የከተማ መንደር ስትራቴጂ ይባላል። ይህ ስትራቴጂ በተመረጡ የከተማ ማዕከላትና መንደሮች ስለሚሰሩ አዲስ መኖሪያ ቤቶችና ስራዎች፣ እንዲሁም በማምረቻና ኢንዱስትሪ ማዕከላት (MIC) በሚካሄደው የኢንዱስትሪ ስራ ላይ ያተኩራል።

የከተማ መንደር ስትራቴጂው በእድገት ላይ በማተኮር ረገድ ውጤታማ ነው። ባለፉት 10 ዓመታት ውስጥ 83% ያክሉ አዲስ መኖሪያ ቤቶች የተሰሩት በከተማ ማዕከላት ወይም መንደሮች ውስጥ ሲሆን ግማሽ ያክሉ መኖሪያ ቤቶች የተገነቡት በDowntown፣ South Lake Union, First Hill፣ እና Capitol Hill ነው። ይህ አቀራረብ የመኖሪያ ቤቶች፣ ቢሮዎችና የችርቻሮ ንግድ ቤቶች ልማት እርስ በርስ በትራንዚት በሚገናኙ በትንሽ ጠባብ፣ በእግር ጉዞ በሚያልቁና፣ የተለያዩ ግልጋሎቶች በሚይዙ መኖሪያ መንደሮች እንዲሰሩ መመሪያ በመስጠት አገልግሏል።

በተመሳሳይ ከከተማ መንደር ወሰኖች ውጪ የሚገኙ የተለያዩ የመኖሪያ መንደሮች እራሳቸውን ችለው ከተሰሩ የመኖሪያ ቤቶች ውጭ ያሏቸው የመኖሪያ ቤት አማራጮች ጥቂት ናቸው። ባለፉት 10 ዓመታት ውስጥ ከእነዚህ የመኖሪያ ቤቶች ዋጋዎች በአስገራሚ ሁኔታ እየጨመረ ከመምጣቱ ጋር ተያይዞ እነዚህ የመኖሪያ መንደሮችም ለአብዛኞቹ የራሳቸው መኖሪያ ቤቶች ለሌሏቸው ሰዎች ለመድረስ ሩቅ ሆነዋል። የከተማ መንደር ስትራቴጂ በተጨማሪም በዋናነት አፓርታማዎችና የንግድ ቤቶች በሚሰሩባቸው የተከለሉ ቦታዎች ላይ የሚያተኩር በመሆኑ ምክንያት በከተማ መንደሮች ውስጥ ያስገኘው አዲስ የመኖሪያ ቤት ባለቤትነት ጥቂት ነው።

## ዋና ዋና ጉዳዮች

የመኖሪያ ቤት አቅርቦትና የዋጋ ተመጣጣኝነት

መፈናቀልና የመኖሪያ መንደር ተደራሽነት

የንግድና ኢንዱስትሪ ልማት

ዕድገትን ከከተማ ኢንቨስትመንቶች ጋር ማስማማት

በከተማው እንደተካሄደው የዘር ዕኩልነት ትንተና አንድ ክፍል ብዙዎቹ ተሳታፊ የሆኑ ነዋሪዎች የከተማ መንደር ስትራቴጂው የተለየ ቀለም ያላቸው ሰዎች አቅማቸው ፈቅዶ ሊኖሩ የሚችሉበትን በታ የገደቡት የታሪካዊ አግላይ ፖሊሲዎችና አሰራሮች አካሄድ ያስቀጠለ እንደሆነ ጠቁመዋል። ከተማው ለአግላይ የመኖሪያ ቤት አሰራሮች አስተዋጽኦ የሚያደርጉና የBIPOC ማህበረሰቦችን የመፈናቀል ጫናዎች የሚጨምሩ ፖሊሲዎችን መርምሮ ማሻሻያ ማድረጉን ይቀጥላል።

ለወደፊት ሲያትል ከፍተኛ የመኖሪያ ቤትና የስራ ዕድገት ማየቱን እንደሚቀጥል ይጠበቃል። የክልሉ የእቅድ ዝግጅት ፖሊሲዎች ሲያትልን በ2044 ዓ.ም ቢያንስ 169,500 አዲስ የስራ ዕድሎችን ለመፍጠር እና 112,000 አዲስ መኖሪያ ቤቶች መስራት እንዳለበት ይጠይቃሉ። በዕድገት ስትራቴጂያችን ላይ ማሻሻያ ማድረግ የመኖሪያ ቤቶች አቅርቦትን፣ አይነትና የዋጋ ተመጣጣኝነትን እንድናሳድግ እና እድገቱ የበለጠ ዕኩልነትና ዘላቂነት የሰፈነበት ከተማ የመፍጠር ሀሳቡን የሚደግፍ መሆኑን እንድናረጋግጥ ሊረዳን ይችላል።

የከተማው ካውንስል የአጠቃላይ እቅድ ማሻሻያውን የተለያዩ የእድገት ስትራቴጂዎችን እንደምናጠናበት እድል እንድንጠቀምበት ኃላፊነት አዞናል።

**እነዚህም የሚከተሉትን ያጠቃልላሉ:**

- አዳዲስ የከተማ ማዕከላትን ወይም መንደሮችን መጨመር
- ከከተማ መንደሮች ውጭ በሚገኙ የመኖሪያ መንደሮች ውስጥ በሚገኙ ቦታዎች እንደ ዱፕሌክስ ወይም ትሪፕሌክስ የመሳሰሉ ብዙ የተለያዩ የመኖሪያ ቤት አማራጮች እንዲኖሩ ማስቻል
- ተጨማሪ ሰዎች ወደ አካባቢ ሱቆችና አገልግሎቶች በእግር፣ በብስክሌት ወይም ፈጣን የአውቶቡስ ራይድ በመጠቀም መድረስ የሚችሉባቸው የተሟሉ የመኖሪያ መንደሮችን ማሳደግ
- ስለ ትራንዚት ዙሪያ ተጨማሪ ዕድገት ማቀድ
- የቤተሰቦችና የንግድ ድርጅቶች መፈናቀልን የሚቀንሱ ስትራቴጂዎች

## አሁን ምን እየሰራን እንደሆነ

- [የከተማ መንደር ስትራቴጂ የዘር እኩልነት ትንተና]
- [የመኖሪያ ቤት ገበያን በገበያ ተመን በሚመራ የመኖሪያ ቤት ፍላጎት እና አቅርቦት ትንተና አማካኝነት መረዳት]
- [ማህበረሰቡን በመኖሪያ ቤት ምርጫዎች ኢኒሺየቲቫችን አማካኝነት በመኖሪያ ቤት ጉዳዮች ላይ ማሳተፍ]
- [በተመጣጠነ ልማት አማካኝነት የመፈናቀል ጫናዎችን]
- [ለመቀነስ፣ ማህበረሰቡን ለማረጋጋት እና የኢኮኖሚ ዕድል ለመፍጠር በማህበረሰብ አነሳሽነት የሚካሄዱ ፕሮጀክቶችን በገንዘብ መደገፍ]

## እስኪ ሥለ ወደፊት እንነጋገር

ተጨማሪ መኖሪያ ቤቶች የት ተሰርተው ማየት ይፈልጋሉ?

ተጨማሪ የንግድ፣ የቢሮ ቦታና የኢንዱስትሪ ልማት የት ተሰርተው ማየት ይፈልጋሉ?

ዕድገቱን እንዴት አሁን ያሉ ቤተሰቦች፣ የንግድ ድርጅቶችና ተቋማትን መፈናቀልን በሚቀንስ መልኩ ልናደርገው እንችላለን?

አስተያየቶችዎን ለሚከተለው ይላኩ:
**oneseattlecompplan@seattle.gov**

ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት የሚከተለውን ይጎብኙ:
**seattle.gov/opcd/one-seattle-plan**

ይህን ሰነድ በተለዋጭ ፎርማት ወይም ቋንቋ ለማግኘት oneseattlecompplan@seattle.gov ን ያነጋግሩ፤ ለዝግጅት ወይም ስብሰባ የአካል ጉዳተኞች አገልግሎት በመጀመሪያ ዕድልዎ ለመጠየቅ oneseattlecompplan@seattle.gov ን ያነጋግሩ።



የOne Seattle አጠቃላይ እቅድ


# ትራንስፖርት

የሚሄዱበት ቦታ የትም ይሁን ምን - ወደ ስራ ወይም ትምህርት ቤት፣ ጓደኞችን መጎብኘት፣ ወደ ስራ ቦታዎች፣ ወደ ቤተ ሙከራዎ፣ ወይም ወደ እራት - ደህንነትዎ ተጠብቆ፣ ውጤታማና ወጪ ቆጣቢ በሆነ መልኩ መሄድ አለበት።

የከተማው ሰራተኞች ጉድጓዶችን ከመሙላትና አውቶቡሶችና ጭነት አቅራቢ ተሽከርካሪዎችን ሰዓታቸውን ጠብቀው እንዲደርሱ ከመርዳት ባለፈ መንገዶችን ይጠርጋሉ፣ የትራፊክ ምልክቶችን ያስተካክላሉ፣ አዝናኝ የማህበረሰብ መሰብሰቢያ ቦታዎችን ያዘጋጃሉ እንዲሁም በሁሉም የእድሜ ደረጃ ላይ ለሚገኙ ሰዎችና አካል ጉዳተኞች የሚያገለግሉ የብስክሌት መንገዶችና የእግር መንገዶችን ይገነባሉ።

እስከ አሁን ድረስ ይዘጋጁ የነበሩት የመንግስት ዕቅዶች ብዙ ሰዎችን በተለይም ጥቁሮችን፣ ነባር ተወላጆችን ወይም በከፊል በቀለም የተለዩ ማህበረሰቦችን፤ LGBTQIA+ ሰዎችን፣ በድህነት ውስጥ የሚኖሩ ሰዎችን፣ ስደተኛ ማህበረሰቦችን እና በቤት ውስጥ እንግሊዝኛ ቋንቋን የማይናገሩ ሰዎችን፣ በእድሜ የገፉ አዋቂ ሰዎችን እና አካል ጉዳተኞችን የሚያገሉ ነበሩ። የጋራ የትራንስፖርት ራዕያችንን ስናዘጋጅ የእያንዳንዱን ሰው ሀሳብ መስማት እና የማህበረሰቡን ፍላጎቶች ማሟላታችንን ማረጋገጥ እንፈልጋለን።

**የሲያትል ቤተሰቦች እንዴት እንደሚ ጓጓዙ**




## በአጠቃላይ የእቅድ ማሻሻያ ስር ለትራንስፖርት የተሰጠው ትኩረት

ዕቅዱ የከተማዋን የእንቅስቃሴ ፍላጎቶች የሚያሟላ እና የአየር ንብረት፣ ደህንነትና እኩልነት ግቦቻችንን ወደማሳካት የሚወስድ የትራንስፖርት ስርዓት ሰፊ የፖሊሲ መመሪያን የሚይዝ ክፍል አለው። የእግር ጉዞን፣ የብስክሌት፣ የትራንዚት ጉዞን እና የጭነት እንቅስቃሴን ለሚጠቅሙ ማሻሻያዎች ድጋፍ በማድረግ የመላውን ሲያትል እድገት እናቅዳለን። ከሲያትል የትራንስፖርት እቅድ ጋር በተመሳሳይ ጊዜ በአጠቃላይ ዕቅዱም ላይ ማሻሻያ እየተደረገበት ሲሆን እቅዱ የጋራ የትራንስፖርት ራዕያችንን ለማሳካት ስለምንወስዳቸው ስትራቴጂዎችና እርምጃዎች የተመለከቱ ተጨማሪ ዝርዝሮችን ያቀርባል።

## ዋና ዋና ጉዳዮች

**የትራንስፖርት አገልግሎት ዕኩልነት**



**የተጓዦች ምቾት/ ደህንነት**



**የአየር ንብረት ተጽእኖዎች**



**የተጨማሪ የጉዞ አማራጮች ተደራሽነት**



## አሁን ምን እየሰራን እንደሆነ

- [የሲትል የትራንስፖርት እቅድ] – ለእያንዳንዱ ሰው አስተማማኝ፣ ውጤታማ እና ተመጣጣኝ ዋጋ ያላቸው አማራጮች ማቅረብ።
- [ቀልጣፋ የትራንዚት ቅንጅት] – በአዲስ የመብራት ሀዲድ ጣቢያዎችና የጣቢያ አካባቢዎች ላይ የሚካሄድ የአካባቢ
  ትንተናና የማህበረሰብ ተሳትፎ።
- የሲያትል [ወቅታዊ ፕሮጀክቶችና ፕሮግራሞች] ሲያትልን ወደፊት ለማስቀጠል በከፊል በድምጽ በሚጸድቅ [የድርሻ ተጣይ በገንዘብ ይደገፋሉ]
  እንዲሁም [የሲያትል የትራንዚት እርምጃ]።

## እስኪ ሥለ ወደፊት እንነጋገር

በከተማው ዙሪያ ለመንቀሳቀስ ምን ተግዳሮቶች ያጋጥሙዎታል?

ምን አማራጮች በመኪና ብቻ የሚሄዱባቸውን ጉዞዎች ለመቀነስ ይረዳሉ?

ከተማው ለእያንዳንዱ ሰው
የበለጠ እኩል የትራንስፖርት አገልግሎት አማራጮችን
ለማቅረብ ምን እርምጃዎችን ሊወስድ ይችላል?

በእግር፣ በመስፈንጠሪያ፣ በብስከተሌት በሚሄዱበት፣ ትራንዚት በሚይዙበት ወይም በሚያሽከረክሩበት ወቅት ደህንነት፣ ምቾትና በራስ መተማመን እንዲሰማዎት ለማድረግ ምን ያስፈልጋል ብለው ያስባሉ?




አስተያየቶችዎን ለሚከተለው ይላኩ:
**oneseattlecompplan@seattle.gov**

ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት የሚከተለውን ይጎብኙ:
**seattle.gov/opcd/one-seattle-plan**

ይህን ሰነድ በተለዋጭ ፎርማት ወይም ቋንቋ ለማግኘት oneseattlecompplan@seattle.gov ን ያነጋግሩ፤ ለዝግጅት ወይም ስብሰባ የአካል ጉዳተኞች አገልግሎት በመጀመሪያ ዕድልዎ ለመጠየቅ oneseattlecompplan@seattle.gov ን ያነጋግሩ።

Seattle

## የOne Seattle አጠቃላይ እቅድ

# የኢኮኖሚ እድገት

ሲያትል የፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ማዕከል ከመሆኑም በተጨማሪ መሪ የዌስት ኮስት የፈጠራ ኢኮኖሚ መዳረሻ ማዕከል ነው። የባህር ትራንስፖርት፣ ኢንዱስትሪ፣ ቴክኖሎጂ፣ የአየር ጉዞ፣ አጠቃላይ ጤና እና ሌሎች ዘርፎች እነዚህ ሁሉም በመጪዎቹ ዓመታት ውስጥ ከፍተኛ የስራ ቅጥር እንዲሚፈጥሩ ይጠበቃል። መጠነ ሰፊ ኢኮኖሚያችን የቅርቡን አለም አቀፍ ወረርሽኝና ከፍተኛ የዋጋ ንረት ጨምሮ በቅርብ ያጋጠሙ ማሽቆልቆሎችን እንድንቋቋም ረድቶናል።

ከተማው የቤተሰብ የመኖሪያ ክፍያ ለሚያስገኙ ስራዎች የሚያስፈልጉ ክህሎቶችን ለማጎልበት ለሚፈልጉ ሰራተኞች አዳዲስ እድሎችን ለማዘጋጀት ከአሰሪዎች፣ ትምህርት ቤቶችና ሌሎችም ጋር በጋራ መስራቱን ይቀጥላል። ለአነስተኛ የንግድ ድርጅቶችና በማደግ ላይ ለሚገኙ የመኖሪያ መንደር የንግድ ስራ ዲስትሪክቶች የምናደርጋቸውን ድጋፎች ማሳደግ እንፈልጋለን። ከተማው ለኪነ ጥበብ ድርጅቶች የሚያደርገው ድጋፍም ለከተማው ኢኮኖሚ እድገትና የባህል አኗኗር ወሳኝ ነው። አሁንም ሆነ ወደፊት የስራዎችና የንግድ ስራ ዕድሎችን ለሁሉም ሰው እኩል ተደራሽነትን ለማሳደግ እንሰራለን።

## በአጠቃላይ ዕቅዱ ስር ለኢኮኖሚ እድገት የተሰጠው ትኩረት

የኢኮኖሚ እድገትን የተመለከተው ክፍል ከሰራተኛ ሀይል ልማት፣ ለመኖሪያ መንደር የንግድ ስራ ዲስትሪክቶች የሚደረግ ድጋፍና እድገት፣ በማደግ ላይ ያሉና አዲስ የሚፈጠሩ ኢንዱስትሪዎች ጤናማ ምህዳርን ማስቀጠል፣ እና የከተማውን የኢንዱስትሪና የባህር ትራንስፖርት ዘርፎች የተወዳዳሪነት ጥቅም መደገፍ ጋር የተያያዙ የከተማውን ፖሊሲዎች ይመራል። ማሻሻያው የሁሉንም ነዋሪዎች እና በተለይም የሲያትል እያደገ ያለ ኢኮኖሚ ጥቅሞች እኩል ተጠቃሚ ያልሆነ የBIPOC ማህበረሰቦችን የመኖሪያ ገቢ ለሚያስገኙ ሙያዎች እኩል ተደራሽነት የሚያረጋግጡ ፖሊሲዎችን ያካትታል።

## ዋና ዋና ጉዳዮች

**የአነስተኛ የንግድ ድርጅቶች የስራዎችና የኢኮኖሚ ዕድሎች እኩል ተደራሽነት**




**ለመኖሪያ የላብ ዋጋ ማግኛ ሙያዎች መገኘት በር የሚከፍት የስራ ስልጠና አዲስ ዕድሎች**



**የኢኮኖሚ እድገት ምንጮ ለሆኑ ለዋና የኢንዱስትሪ ዘርፎች የሚደረግ ድጋፍ**



**ለኪነ ጥበብና የባህል ድርጅቶች ድጋፍ ማድረግ**



## አሁን ምን እየሰራን እንደሆነ

- [የሲያትል የኢንዱስትሪና የባህር ስትራቴጂ]
- [የንግድ የዋጋ ተመጣጣኝነት]
- [የሰራተኛ ሀይል ልማት]
- [ለመኖሪያ መንደር የንግድ ስራዎች ድጋፍ ማድረግ]
- [ቁልፍ/ ዋና የኢንዱስትሪ ድጋፍ]

## እስኪ ሥለ ወደፊት እንነጋገር

እኩል የስራዎች ተደራሽነትን
እንዴት በተሻለ ሁኔታ ማረጋገጥ እንችላለን?

በመላው የሲያትል መኖሪያ መንደሮች ውስጥ
የሚገኙ የንግድ ስራ ዲስትሪክቶች እንዴት
መበልጸግና ማደግ ይችላሉ?

ነዋሪዎችን ሙያዎች እንዲያገኙ ለመርዳት የስራ ስልጠና
ፕሮግራሞችን እንዴት ማዘጋጀት እንችላለን?




አስተያየቶችዎን ለሚከተለው ይላኩ:
**oneseattlecompplan@seattle.gov**

ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት የሚከተለውን ይጎብኙ:
**seattle.gov/opcd/one-seattle-plan**

ይህን ሰነድ በተለዋጭ ፎርማት ወይም ቋንቋ ለማግኘት oneseattlecompplan@seattle.gov ን ያነጋግሩ፤ ለዝግጅት ወይም ስብሰባ የአካል ጉዳተኞች አገልግሎት በመጀመሪያ ዕድልዎ ለመጠየቅ oneseattlecompplan@seattle.gov ን ያነጋግሩ።